# የያዕቆብ ውበት ቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልና

“ለርስቱ እኛን መረጠን፥ የያዕቆብን ውበት የወደደ።”

[ምስጢሩን በአፌ እንዲገልጽ፤ ስለ ቅድስት ማርያም ድንግልናም እንድቆም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እጣራ ዘንድ ይገባል። ‘ለዘጠኝ’ ወር የኖረበትን የተቀደሰ ማረፊያ የሆነውን ማህጸን ከሌሎች ጥርጣሬዎች የጠብቅ ዘንድ እግዚአብሔር ወልድን እጣራ ዘንድ ይገባል። እንዲሁም ከሙሽርነት በፊት እናት የሆነች ከወለደች በኋላም ድንግል ሆና የኖረችውን የልጁን እናት ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር አብንም ደግሞ እለምን ዘንድ ይገባል።] ቅዱስ ጄሮም

[I must call upon the Holy Spirit to express His meaning by my mouth and defend the virginity of the Blessed Mary. I must call upon the Lord Jesus to guard the sacred lodging of the womb in which He abode for ten months from all suspicion of sexual intercourse. And I must also entreat God the Father to show that the mother of His Son, who was a mother before she was a bride, continued a Virgin after her son was born.] st. Jerome, perpetual virginity of blessed Mary

ወንድም አክሊል

ይዘት፡

1. ድንግል ማርያም ከዮሴፍ ጋር ተጋብቷል..??
2. እጮኛዋ ለምን ተባለ..??
3. የበኩር ልጇን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ነበር
4. ወንድሞቹስ..??
5. ስትወልድ ድንግልናዋን አጣችው..??

ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልና ጋር በተያያዘ ኑፋቄ ትምህርቶች የተጀመሩት አሁን ሳይሆን ይልቁንም ቀደም ሲል በ4ኛው ክ/ዘመን ገደማ ነው። በዚህ ኑፋቄው የሚታወቀውም ሄልቪድዩስ(Helvidius) ነበር። ሄልቪዲዩስ ሮም ውስጥ የነበረ ሰው ሲሆን በሰዓቱ ደግሞ እዛው ሮም ውስጥ ለሄልቪድዩስ ኑፋቄ መዶሻ የሆነ ጀሮም የተባለ ታላቅ አባት ነበር። against Helvidius(The perpetual virginity of Mary)[1]; ጀሮም ለሄልቪድዩስ መልስ የሰጠበት መጽሃፉ ነው። አሁን ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ሁሉ ከሄልቪድዩስ የመጡ ናቸው። እኛም እነዚህን ጥያቄዎች እያነሳን ከአባቶችም እያደረግን መልስ ለመስጠት እንሞክራለን አምላክ ይርዳን።

[1] http://www.newadvent.org/fathers/3007.htm

***ጥያቄ 1.*** *ለዮሴፍ ታጭታ የነበረው እንዲጋቡ ነው ክርስቶስን ከወለደች በኋላም ተጋብተው ኖረዋል.. ሉቃ 1፡27 "ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።"*

**መልስ፡** እመቤታችን ለዮሴፍ ታጭታ እንደነበር ግልጽ ነው.. አላማው ግን ምን ነበር..?? እውነት እንዲጋቡ ነው..?? ተጋብተዋልስ..?? የሚሉ ጥያቄዎችን ስናነሳ መጽሃፍ ቅዱስ ለናሙና ያህል አንድም ቦታ እንደተጋቡ አይናገርም፤ ይህም የሆነው አስቀድሞም ዮሴፍ እጮኛ የተባለው ለተለየ አላማ ስለነበረ ነው። አላማው ምን ይሆን..?? የሚለውን ነገር ከማየታችን በፊት ግን እስቲ ድንግሊቱና ዮሴፍ ፈጽሞ ሊጋቡ የማይችሉባቸውን ሶስት መሰረታዊ ነገሮች እናንሳ፡-

1. ትንቢት ስለተነገረላት፡ "እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ 'ይህች በር ተዘግታ ትኖራለች እንጂ አትከፈትም፤ ሰውም አይገባባትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶባታልና ተዘግታ ትኖራለች' "(ሕዝ 44፡2) እግዚአብሔር አምላክ ለነቢዩ ወደፊት ስለሚነሳው ቤተ መቅደስ ያሳየዋል "ወደ መቅደሱም መዝግያ መለሰኝ፤ እነሆም ውሃ ከቤቱ መድረክ በታች ወደ ምስራቅ ይወጣ ነበር.."(ሕዝ 47) ይህ ውሃ የሚፈስበት ቤተ መቅደስ እንደ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ አይነት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይልቁንም ያ መቅደስ ክርስቶስ ነበር.. ጌታ ኢየሱስ በዮሃ 7፡38 ላይ "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ" ብሎ ተነጋረ። ታድያ ግን መጽሃፍ በዚህ መልኩ የቱ ጋር እንደተናገረ ስንመረምር ሕዝቅኤል ላይ ስላለው ከመቅደሱ ስር ስለሚፈልቀው ምንጭ እንደተናገረ እንረዳለን። በግልጽም ሲመሰክር እንዲህ አለ "ጌታችን ኢየሱስም 'ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ በሦስተኛውም ቀን አነሳዋለው' ብሎ መለሰላቸው.......... እርሱ ግን ይህን የተናገረው **ቤተ መቅደስ ስለተባለ ሰውነቱ** ነበር።" (ዮሃ 2፡ 19-21) ይህ ስጋው መቅደስ የተባለው ደግሞ በስጋዌ ወይም በተዋህዶ ሰዓት ነው "ቃልም ስጋ **ሆነ**፤ በእኛም **አደረ**" እንዲል(ዮሃ 1፡14)። ይህን ቤተ መቅደስ የተባለውን ስጋውን የወሰደው ደግሞ ከእመቤታችን ሲሆን የተዋሃደውም እዛው የእናቱ ማህጸን ውስጥ ነው። ስለዚህም ሕዝቅኤል ተዘግታ ያያት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የገባባት በር የኢየሱስ እናት ማርያም እንደሆነች በዚህ አወቅን ማለት ነው። ለዛም ነው የጥንት አባቶችም ይህንን የሕዝቅኤልን ትንቢት ከእመቤታችን ጋር አገናኝተው የሚተረጉሙት። ጀሮም ክርስትና አንድ[2] በነበረችበት ሰዓት የነበረው አባት እንዲህ አለ፡ [Mary is "a garden enclosed…a fountain sealed"(song 4:12), She is the east gate, spoken of by the prophet Ezekiel, always shut and always shining…. and through her the Sun of Righteousness, our high priest after the order of Melchizedek, goes in and out.][3] [ማርያም የተቆለፈች ገነት፣ የተዘጋች ገነት፣ የታተመች ጉድጓድ ናት(መሓ 4፡12)… ተዘግታ የምትኖር በነቢዩ ሕዝቅኤል የተነገረች የምስራቅ በር ናት፤ በእርሷም እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ዘላለማዊ ሊቀ ካህናችን የሆነው(ዕብ 5፡10) ጸሃየ ጽድቅ(ሚል 4፡2) ገባ፤ ወጣም]

---

[2] አሁንም ክርስትና አንድ ብቻ እንደሆነች እናምናለን። በክርስትና ስም ሌሎችም ሳይመጡ የሚለውን ላማመልከት ነው

[3] St Jerome, letter 48 to Pammachius, 21

ስለዚህም የእስራኤል አምላክ ክርስቶስ ኢየሱስ ገብቶባታልና ተዝግታ ትኖራለች እንጂ ማንም አይገባባትም።

2. እመቤታችን ራሷ በአንደበቷ ወንድ ላለማወቅ መወሰኗን መስክራለችና፡ መልአኩ ልጅ እንደምትወልድ ሲያበስራት ማርይም ድንግል የተናገረችው ቃል አንድ ትልቅ ውሳኔ እንደነበራት የሚያሳይ ነው፤ መልአኩ እንዲህ ይላታል፡ "እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። .... ማርያምም መልአኩን። **ወንድ ስለማላውቅ** ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።" (ሉቃ 1፡31-34) እዚሁ የወንጌል ክፍል ላይ ከቁጥር 26 ጀምሮ እንደሚገልጸው መልአኩ የተላከው እጮኛ ወዳላት ሴት ነው። እጮኛ ያላት ሴት "ልጅ ትወልጃለሽ" ስትባል እጮኛ ስላላት ከእርሱ እንደምትወልድ አውቃ አሜን ማለቷ አይቀርም። እመቤታችን ግን ምንም እንኳን እጮኛዋ የተባለ ወንድ ቢኖርም "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?" ብላ መለሰች። እጮኛ እንዳላት ረስታው ይሆን..?? ለዚህ ነው ክርስትና አንድ በነበረችበት ሰዓት የነበረው አውግስጢኖስ እንዲህ የሚለው [ድንግልናዋን ጠብቃ ለመኖር አስቀድማ ለአምላኳ ቃል ባትገባማ "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?" ብላም ባልተናገረች ነበር] ["How," says she, "shall this be, seeing I know not a man?" Which assuredly she would not say, unless she had before vowed herself unto God as a virgin.][4] ከዚህ የምንረዳው ድንግሊቱ እናት አስቀድማም ለዮሴፍ የታጨችው ለጋብቻ አለመሆኑን ነው።

3. ዮሴፍና ማርያም የቅርብ የስጋ ዘመዶች ስለሆኑ፡ ጌታ ኢየሱስ የዳዊት ዘር ስለመሆኑ ከአብርሃምም እንደመጣ መጽሃፍ ቅዱስ በስፋት ይገልጻል። ማቴዎስ ወንጌሉን ሲጀምር "የዳዊት ልጅ፤ የአብርሃም ልጅ፤ የጌታ ኢየሱስ የልደት መጽሃፍ" ይላል። ይህ የዳዊት ሥርና ዘር የሆነው(ራዕ 22፡16) ጌታ ደግሞ የተወለደው ከሴት ብቻ ነው። "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ" (ገላ 4፡4)። እነዚህን ሃሳቦች እንያዝና ወደ ክርስቶስ የዘር ሃረግ ቆጠራ እስቲ እንመለስ "የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ................. ኤልዩድም አልዓዛርን ወለደ፤ አልዓዛርም ማታንን ወለደ፤ ማታንም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ።" (ማቴ 1፡1-16) እዚህ የዘር ሃረግ ላይ እንደምንመለከተው ክርስቶስ የዳዊት ልጅ፤ የአብርሃም ልጅ ተብሎ ይወርድና መጨረሻ ላይ ግን የማርያም እጮኛ የሆነ ዮሴፍን ያስቀምጣል ምንም እንኳን መጨረሻ ላይ ያለው ዮሴፍ ሳይሆን ሴት የሆነችቱ ድንግል ማርያም ብትሆንም። ምክንያቱም ከላይ ግልጽ አድርገን እንደመጣነው ኢየሱስ ከሴት የተወለደ የድንግል ማርያም ልጅ እንጂ ከወንድ የተወለደ የዮሴፍ ልጅ አይደለም። ሁለት ነገሮችን እናንሳ፤ *ዮሴፍ ከኢየሱስ ጋር በስጋ አይገናኝም* ካልን የተጻፈው የዘር ሃረግ ሁሉ *ሃሰት* ሊሆን ነው፤ አይ *የስጋ ግንኙነት አላቸው* ካልን ደግሞ "ከሴት ተወለደ፤ ከመንፈስ ቅዱስ ተወለደ" የሚሉ ቃላት *ሃሰት* ሊሆኑ ነው..

[4] St Augustine, on holy virginity, 4

እንመለስ ተወዳጆች፤ አላዋቂነትን የጥበብ አምላክ እርሱ በጥበቡ ያርቅልን **ሃሰት የሚባል ነገር የለም** ዮሴፍ አዎ ከክርስቶስ ጋር በስጋ ይገናኛል ይህ የሆነው ግን ጌታ ከእርሱ ተወልዶ ሳይሆን ከወለደችው ከድንግሊቱ ማርያም ጋር ዝምድና ስላለው ነው። ጀሮምም ዮሴፍ ለምን እጮኛዋ እንደተባለ ሲናገር ዘመድ እንደ ሆኑ አንድ ደም እንደሆኑ ተናግሯል ቀጣይ የሚነሳው ጥያቄ ላይ አስቀምጥላችኋለው ምን እንዳለ። በቤተ ክርስትያናችን ዘመዳሞች እነደሆኑ የሚነገረው እንዲሁ አይደለም[5] ዘመዳሞች ከሆኑ ደግሞ መጋባት አይችሉም በእግዚአብሔር ፊትም ሃጢዓት ነውና። "ከእናንተም ማንም ሰው ኃፍረተ ሥጋውን ይገልጥ ዘንድ <u>ወደ ዘመዱ ሁሉ አይቅረብ</u>፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።" (ዘሌዋ 18፡ 6)

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን የበኩር ልጇን ያለው ሌላም ልጅ ቢኖራት ነው የሚሉ ይኖራሉ። ፈገግታን የሚያጭር ጥያቄ ቢሆንም ጀሮም በቀላሉ እንዴት እንደመለሰ እንመልከት፡ "ከሰው ወይም ከእንስሳ ቢሆን፥ ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡት ሥጋ ሁሉ ማኅፀን የሚከፍት ሁሉ ለአንተ ይሆናል፤ ነገር ግን የሰውን በኵራት ፈጽሞ ትቤዠዋለህ፥ ያልነጻውንም እንስሳ በኵራት ትቤዠዋለህ።" (ዘኁ 18፡15) ይህንን ቃል በማንሳት በኩር የሚባለው ማህጸን የሚከፍት ሁሉ እንጂ ግዴታ ተከታይ ያለው ማለት አይደለም ይለዋል። ስለዚህም ምን ይላል [Every only begotten son is a first-born son, but not every first-born is an only begotten][6] [ብቸኛ ልጅ ሁሉ በኩር ነው፤ በኩር ሁሉ ግን ብቸኛ(አንድያ) ልጅ አይደለም]

***ጥያቄ 2፡*** *ታድያ እጮኛዋ ለምን ተባለ..??*

**መልስ፡** ጀሮም፡ ለሦስት ምክንያት ተብሏል ይላል፡- [First, that by the genealogy of Joseph, whose kinswoman Mary was, Mary's origin might also be shown. Secondly, that she might not in accordance with the law of Moses be stoned as an adulteress. Thirdly, that in her flight to Egypt she might have some solace, though it was that of a guardian rather than a husband.][7]

1. የዘር ሃረግ ሲነገር በወንድ ነውና የኢየሱስ ዘር ሃረግ በዮሴፍ በኩል ተነግሮ ተመልክተናል። በዮሴፍ የዘር ሃረግ ደግሞ ዘመዱ(kinswoman) የሆነችው ማርያምን መገኛ(ዘር) ለማሳየት።
2. ሁሉን አዋቂ (omniscient) የሆነው እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞም እመቤታችን እናቱ እንደምትሆን፤ እናት የምትሆነውም በድንግልና እንደሆነ ያውቅ ነበር። ታድያ ግን በአይሁድ ሕግ አንዲት ሴት ባል ሳይኖራት ጸንሳ ብትገኝ በድንጋይ ተወግራ ትሙት(ዘዳ 22፡20) ይባላልና ከዚህ ለመጠበቅ ዮሴፍ እጮኛዋ ይባል ዘንድ የእግዚአብሔር ፍቃዱ ሆነ። ለዛም ነው አይሁድ ኢየሱስ የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸው ነበር የተባለው(ሉቃ 3፡23)። አውግስጢኖስም ይህንኑ አጠናክሮ ይናገራል [But, because the habits of the Israelites as yet refused this, she

[5] ማቴዎስ ወንጌል አንድምታ

[6] St Jerome, The perpetual virginity of blessed Mary 12

[7] Ibid 4

was espoused to a just man, who would not take from her by violence, but rather guard against violent persons, what she had already vowed.][8]

3. ኢየሱስን ከወለደች በኋላም ባል የላትምና በስደቷም በሌሎች ነገሮችም ሁሉ እንዲረዳት እጮኛ ተባለ። ሌላው ከላይ እንዳየነው እመቤታችን በድንግልና ለመኖር ቃል ገብታለችና እሱን ጠብቃ እንድትኖር ከከፉ ወንዶች እንዲጠብቃት አንድም ሌላ ባል ነኝ ብሎም የሚመጣ እንዳይኖር ዮሴፍ ይጠብቃት ዘንድ እሱን ዘመዷን እጮኛ ብላ ተቀመጠች። እጅጉን የተወደደች እናት።

***ጥያቄ 3፡*** "የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው።" (ማቴ 1፡ 25) በዚህ ቃል መሰረት ማርያም ከወለደች በኋላ አዳም ሄዋንን እንዳወቃት(ዘፍ 4፡1) ዮሴፍ ማርያምን አውቋታል የሚል ጥያቄ ነው

**መልስ፡** "ከወለደች በኋላ አውቋታል" እንዲሉ ያደረጋቸው "እስከትወልድ ድረስ" የምትለዋ ሃረግ የጊዜን ወሰን እንደምታመለክት አድርገው መቁጠራቸው ነው።

1. ታላቁ ሊቅ ዮሃንስ አፈወርቅ እንዲህ ይለናል፡ [ወንጌላዊው እዚህ ጋር "እስክትወልድ" ብሎ የተናገረው ከወለደች በኋላ አውቋታል የሚል ጥርጣሬ ውስጥ እንድንገባ ሳይሆን ከመውለዷ በፊት ፍጹም ድንግል መሆኗን ለማስረዳት ብቻ ነው። ነገር ግን "እስክትወልድ" ለምን አለ ሊባል ይችላል፤ ይህ ምክንያቱ ለመጽሃፍ ቅዱስ እንዲህ ባለ ሁኔታ ገልጾ ግን ደግሞ ከጊዜ ወሰን ውጪ ማስቀመጥ ልማዱ ስለሆነ ነው። በመርከቢቷ ላይ ለቁራው እንደተባለው "ቁራውም ውሃው ከምድር ላይ <u>እስኪደርቅ ድረስ</u> አልተመለሰም"(ዘፍ 8፡7) ይህ ማለት ከዛም ቦሃላ አልተመለሰም ማለት ነው፤ "ከዘላለም <u>እስከ ዘላለም</u> መቼም መች አንተ ነህ"(መዝ 89(90)፡2) ሲልም የጊዜ ገደብ እየሰጠ አይደለም፤ "በዘመኑም ጽድቅ ይበቅላል፤ ጨረቃም <u>እስኪያልፍ ድረስ</u> ሰላም ብዙ ነው" በጨረቃ ጊዜ ሰላሙን እየገደበ አይደለም። ልክ እንዲሁ አሁንም "እስክትወልድ" ሲል የጊዜ ወሰንን የሚያመለክት አይደለም። ከወለደች በኋላማ ዮሴፍ እንደ ሚስት ተቀብሏት ቢሆን ኖሮ ጌታም ሰው አብሯት እንደሌለ ለዮሃንስ ወደ ቤቱ እንዲወስዳት ባላዘዘው ነበር(ዮሃ 19)] [He hath here used the word "till," not that thou shouldest suspect that afterwards he did know her, but to inform thee that before the birth the Virgin was wholly untouched by man. But why then, it may be said, hath he used the word, "till"? Because it is usual in Scripture often to do this, and to use this expression without reference to limited times. For so with respect to the ark likewise, it is said, "The raven returned not till the earth was dried up." And yet it did not return even after that time. And when discoursing also of God, the Scripture saith, "From age until age Thou art," not as fixing limits in this case. And again when it is preaching the Gospel beforehand, and saying, "In his days shall righteousness flourish, and abundance of peace, till the moon be taken away," it doth not set a limit to this fair part of creation................ For if

[8] on virginity 4

he had known her, and had kept her in the place of a wife, how is it that our Lord commits her, as unprotected, and having no one, to His disciple, and commands him to take her to his own home?][9]

2. ወንጌላዊው "አላወቃትም" ሲል አንድም ከእውቀት ጋር ይገናኛል። ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንዲህ ይላል፡ [ዮሴፍ የበኩር ልጇን እስከትወልድ አላወቃትም ማለቱ አምላክ በሆዷ ስላለ የድንግል መልኳ ይለዋወጣልና ነው። መልኩ በሆዷ በተለዋወጠ ጊዜ ከእርሱ ጋር እንደርሱ መልኳ ይለዋወጣል። እንደ ንጹህ ብርሌ መልክ በውስጡ ውሃ ባኖሩበት ጊዜ ውሃ መስሎ እንዲታይ። የወይን ጠጅም ባኖሩበት ጊዜ የወይን ጠጅ መስሎ እንዲታይ፤ በውስጡም ያለ ቀይ ነገር ቢሆን እንዲቀላ፤ ቁጽልጽልም ቢሆን እንዲቁለጸለጽ። ድንግልም እንዲሁ የልጇ መልክ በሆዷ በተለወጠ ጊዜ የእርሷም መልክ ከእርሱ ጋር እንደርሱ ይለወጣል። እንደ ሮማን አበባ የምትቀላበት ጊዜ አለ፤ እንደ ናርዶስ አበባ የምትነጣበት ጊዜ አለ፤ እንደ ጽጌረዳ የምታንጸባርቅበት ጊዜ አለ፤ እንደ ተከል የምትለመልምበት ጊዜ አለ። ከወለደች በኋላ ግን መልኳ አልተለወጠም፤ በመልኩ መለወጥ መልኳን የሚለውጠው ልጇ መለኮት ከእርሷ ከነሳው ትስብእት ጋር ከሆዷ ወጥቷልና።][10]

***ጥያቄ 4*** ፡ የኢየሱስ ወንድሞች የተባሉ አሉ። ያውም ስማቸው ሳይቀር ተጠቅሷል። ኧረ ክርስትያኖች ዝምብላችሁ ነው.. የሚሉም አይጠፉም። "ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም።" (ማቴ 13፡55-56)

**መልስ** ፡ ኢየሱስ አዎ ወንድሞች አሉት። ግን ደግሞ ወንድም ምንድነው የሚለውን ነገር ከመመልከታችን አስቀድመን ሁሌም ማስተዋል ያለብን ሁለት ነገሮችን እናስቀምጥ፡-

1. ለናሙና ያህል አንድም ቦታ ከኢየሱስ ውጪ ሌሎች ሰዎች የማርያም ልጆች ተብለው አልተጠሩም
2. ለናሙና ያህል አንድም ቦታ ድንግል ማርያም ከኢየሱስ ውጪ ለሌላ ሰው እናት ተብላ አልተጠራችም። ቆይ ቆይ አንድ ቦታ አለ እሱም ከመስቀል ስር ለወንጌላዊው ዮሃንስ "እናት ትሁንህ" ብሎ ልጇ ኢየሱስ ሰጥቶታል።(ዮሃ 19፡27)

እነዚህን ሁለት ነገሮች ይዘን ታድያ ለምን ወንድሞች ተባሉ የሚለውን ነገር እንመልከት፡-

- መጽሃፍ ቅዱስን እንደው በጥቂቱ እንኳን አነበብኩ የሚል ሰው አንድ ነገር ያስተውላል፤ ይህም የተለያየ ዝምድና(ግንኙነት) ያላቸው ሰዎች ወንድም ሊባሉ እንደሚችሉ ነው። አሁን እኔ በዝች ትንሽ ጽሁፍ ውስጥ ብዙ ነገር ሳልጠቅስ የአብርሃም እና የሎጥን ምሳሌ ልስጣችሁ፡ "አብራምም ሎጥን አለው። እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ።" (ዘፍ 13፡8) ተወዳጆች አብርሃም ኘ ለሎጥ ወንድሙ ሳይሆን አጎቱ ነው(ዘፍ 14፡12)። እሺ በቃ አንድ ያጣላል ሁለተኛ ልጨምርላችሁ፡- ሃዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ስለመታየቱ ሲናገር እንዲህ አለ፡ "ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ.."(1ቆሮ 15፡6) ወንድሞች ስለተባለ ማርያም ከኢየሱስ ውጪ

---
[9] St john Chrysostom, homilies on the gospel of Matthew, hom. 5
[10] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ አርጋኖን ዘሠሉስ 8፡14-19

ከ500 በላይ ልጆችን ወልዳለች ማለት አይደለም። ይልቁንም በሕብረት ውስጥ ያሉ አብረው የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ወንድሞች ይባላሉ ነው።

- ሌላው ደግሞ በመጽሃፍ ቅዱስ "ሁለተኛዋ ማርያም" ተብላ የተጠራች ማርያም አለች(ማቴ 28፡1) በሌላ ቦታ ደግሞ "የቀለዮጳም ሚስት ማርያም" ተብላም ተጠርታለች(ዮሃ 19፡25) ይህች ማርያም ደግሞ "የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም" በመባል የኢየሱስ ወንድም የተባሉት ያዕቆብና ዮሳ የማርያም ልጆች እንዳልሆኑ ግልጽ ሆነ(ማቴ 27፡56) ማቴዎስ ወንጌሉ ላይ ከመስቀሉ ስር ስለነበሩት የኢየሱስ እናት ማርያም እና ወንጌላዊው ዮሃንስ አልጻፈም። ዮሃንስ ጽፎታል(ዮሃ 19፡ 26)።

  ታድያ ግን የሁለተኛዋ ማርያም ልጆች ሆነው እንዴት የኢየሱስ ወንድም ሊባሉ ቻሉ..?? በተለይ ያዕቆብ ታናሹ እየተባለ ይነገራል እውነትም ያዕቆብ የኢየሱስ ታናሽ ወንድም ነው። እንዴት..?? የሚለውን እንመልከት፡ ይህች ሴት(ሁለተኛዋ ማርያም) የእናታችን የማርያም እህት ተብላለች "ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ፥ የእናቱም እኅት፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር።" (ዮሃ 19፡25) እናታችን ማርያምና የቀለዮጳ ሚስት ማርያም እህትማማቾች ከሆኑ እነ ያዕቆብ ለኢየሱስ ለምን ወንድም እንደተባሉ ግልጽ ነው ማለት ነው። እዚህ ጋር ግን አንድ ጥያቄ ይነሳል እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለእናት ለአባቷ አንድ ናት፤ እህት ከየት አመጣች..?? መጠየቅም ያለበት ጥያቄ ነው፡ ድንግሊቱ ከሁለተኛዋ ማርያም ጋር እህት የተባለችው ቀለዮጳ የዮሴፍ ወንድም ስለሆነ ነው። ከላይ እንደተመለከትነው ደግሞ ዮሴፍ ምንም እንኳን ለእመቤታችን ባል ባይሆንም የስጋ ዝምድና ያለው ሁሌም ይጠብቃት ዘንድ አብሯት ያለ እጮኛዋ ነውና ነው። ሄጌሲፖስ የተባለ ከ110-180 ዓም የኖረ ትልቅ ቅዱስ አባት ዮሴፍና ቀለዮጳ ወንድማማቾች እንደነበሩ መግለጹን አውሳብዮስ(ከኒቂያውም ጉባኤ በፊት የነበረ አባት) የቤተክርስትያንን ታሪክ ሲጽፍ እንዲህ አለ:-

  [ያዕቆብ ሰማእትነትን ተቀብሎ ሲያልፍ የሱን ቦታ ተክቶ ኢየሩሳሌም ላይ ኤጲስ ቆጶስ መሆን ያለበት ማን እንደሆነ በሰአቱ የነበሩ ሃዋርያት እና ደቀመዛሙርቱ ሁሉ ከየአቅጣጫው ተሰባስበው በአንድነት በወንጌል ላይም የተነገረለትን የቀለዮጳን ልጅ ስምኦንን መረጡ። የኢይሱስም አክስት ልጅ ነበረ፤ ሄጌሲፖስ ዮሴፍ የቀለዮጳ ወንድም እንደሆነ መዝግቦ ነበርና።]

  [After the martyrdom of James and the conquest of Jerusalem which immediately followed, it is said that those of the apostles and disciples of the Lord that were still living came together from all directions with those that were related to the Lord according to the flesh (for the majority of them also were still alive) to take counsel as to who was worthy to succeed James. They all with one consent pronounced Symeon, the son of Clopas, of whom the Gospel also makes mention; to be worthy of the episcopal throne of that parish. He was a cousin, as they say, of the Saviour. For Hegesippus records that Clopas was a brother of Joseph.][11]

[11] Eusebius, church history 3: 11

ባይሆን እዚህ ጋር አንድ መታየት ያለበት ነገር አይተን እንለፍ፡ ጌታ ኢየሱስ በስጋው ሰውነት በኩል እኛን መስሏልና ሃዋርያው ጳውሎስ እንዳለን "ወንድሞች ብሎ ሊጠራን አያፍርብንም" እኛ እግዚአብሔርን አባታችን ብለን ልንጠራው የቻልነው ክርስቶስ እርሱ ወንድማችን ስለተባለ ነው። ክርስቶስ የባህሪ ልጁ ሲሆን እኛ ግን የጸጋ ነን። ታድያ ክርስቶስ አባት ብቻ አይደለም እናትም አለው። ታድያ እናታችን ብለን የማንጠራት ትእቢት ይሆን..?? የአምላካችንን እናት እኮ የእኛ እናት ማለት ለእኛ ተግብቶን አይደለም፤ ግን ደግሞ በመስቀል ላይ ራሱን ሰጥቶን ፍቅሩን የገለጸልን ጌታ ከመስቀል ሥር ደግሞ እናቱንም ስለሰጠን እናታችን እንላታለን። ስጦታችን ናት ድንግል።

***ጥያቄ 5*** **፡** ኧረ ኡኡ በቃ እሺ ማርያም ዮሴፍን አላገባችውም ሌሎች ልጆችም አልወለደችም፤ ግን ደግሞ ኢየሱስን ስትወልደው ድንግልናዋን አጥታዋለች። መቼስ ኢየሱስ ስጋና አጥንት የለውም አትሉንም..??

**መልስ፡** ጄሮም ይህንንም ጥያቄ ሲመልስ በአጭሩ እንዲህ ነበር ያለው፡ [ክርስቶስ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ፥ በመንፈስ ያልሆነ እጁንና ጎኑን አሳይቶ አስዳሶ፥ በሥጋ በተዘጋ በር ከፈቱልኝ ሳይል ወደ ሃዋርያቱ እንዴት እንደገባ ስትነግረኝ እኔ ደግሞ የተዘጋውን የድንግልን በር እንዴት ሳይከፍት እንደወጣ ወይም ቅድስት ማርያም እንዴት በአንድ ጊዜ እናትም ድንግልም እንደምትሆን እነግርሃለው።]

[Let my critics explain to me how Jesus can have entered in through closed doors when He allowed His hands and His side to be handled, and showed that He had bones and flesh, thus proving that His was a true body and no mere phantom of one, and I will explain how the holy Mary can be at once a mother and a virgin.][12]

አባ ጊዮርጊስም እንዲህ አለ፡ [ሦስቱን ደጆች ያልከፈተ የአብን ልጅ ጥበቡን አደንቃለሁ። ያለመለወጥ በህቱም ድንግልና በመወለዱ፤ የመቃብሩን ደጅ ሳይከፍት ተዘግቶ ሳለ ተንስቶ በመውጣቱ፤ የቤቱም ደጅ ተዘግቶ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው ወዳለበት ገባ። ሳይከፈትም ወጣ። ስለዚህም ሦስት ደጆጅ ልቤ አደነቀች።][13]

- [የማይወሰነው እንዴት ተወሰነ? ሁሉን የያዘ እርሱ እንዴት በመሃጸን ተያዘ፤ ከሴትም ተወለደ? ድንግል ወልዳ እንዴት በድንግልና ኖረች..??] ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅ[14]

[12] St Jerome, letter 48 21

[13] አርጋኖን ዘቀዳሚት 3:7-8

[14] john chrysostom Hom. In Matt. 4:3

ከእዝች ትንሽ ጽሁፍ ውስጥ ምን እንረዳ..??

## ክርስቶስ እርሱ፡

## በመለኮት ለአብ አንድያ የበኩር ልጁ ነው።

## በሥጋ ለማርያም አንድያ የበኩር  ልጇ ነው።

## ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ለእናቱም ለአባቱም **አንድ** ነው።

በቀጣይ እንደ አምላክ ፍቃድ የእመቤታችንን ድንግልና ከድህነታችን ጋር እንዴት እንደሚገናኝና በድህነታችን ውስጥ ያለውን የእርሷን ሚና ልክ እንደዛሬው ከብዙ በጥቂቱ ቆንጥረን ለማየት እንሞክራለን

አምልኮ ለብቻው የሚገባው የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ሰው የሆነው የቅዱስ ሚካኤል ጌት ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ መንፈሱ ይጎብኘን።[i]

---

[i] የአባቶችን መጽሃፍት በነጻ ኢንተርኔት ላይ ታገኛላችሁ http://www.newadvent.org/fathers/
ጥያቄ ወይም አስተያየት ቢኖራችሁ ቴሌግራም ላይ @aklili ብላችሁ አግኙኝ

ወንድም አክሊል